Park Hill School District
Building Successful Futures • Each Student • Every Day

# የመድሐኒት አጠቃቀም መመሪያ እና የፍቃድ ቅጽ

**<u>በትምህርት ቤት ለተማሪዎች የሚሰጥ መድሐኒት</u>**

በትምህርት ሰአት መድሐኒት ለተማሪዎች የሚሰጠው እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ከትምህርት ሰአት በፊት እና በኋላ ዶዞች እንዲሰጥ የሚያስችል ጊዜ ሰሌዳን እናበረታታለን፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ቀጥሎ በተቀመጠው ጊዜ ሰሌዳ የህክምና ባለሙያዎች ለልጅዎ በትምህርት ቤት መድሐኒት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከትምህርት ቤት ነርስ ውጪ የሆኑ ግለሰቦች መድሐኒት ለልጅዎ የሚሰጡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል(በመስክ ጉዞ በምሳ ሰአታት ወዘተ)፡፡ እነዚህ ሰራተኞች ስልጠና ያገኙ እና በነርስ መመሪያ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡

**<u>የመድሐኒት አጠቃቀም</u>**

1. በትምህረት ቤት ቆይታ ለተማሪዎች ለሚሰጡ ሁሉም መድሐኒቶች የመድሐኒት ፈቃድ ቅጽ መሙላት እና በወላጅ/አሳዳጊ ሊፈረም ይገባል፡፡ **<u>የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ መድሐኒት አይሰጥም</u>**

2. በሀኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ ሁሉም መድሐኒቶች ላይ በሀኪም/ፋርማሲስት የተጻፈው አወሳሰድ የሚገልጽ ጽሁፍ ሊለጠፍበት ይገባል፡፡ ይህም በትምህርት ቤት የሚወሰድ ኢንሄለርን ይጨምራል፡፡ ጽሁፉ በኢንሄለር ላይ ሊለጠፍ ይገባል ወይም ኢንሄለሩ ከእነ ማሸጊያው ይዞ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ይገባል፡፡

3. ማናቸውም ያለ ሀኪም ማዘዣ የሚወሰዱ መድሐኒቶች በኦሪጅናል ማሸጊያቸው ሆነው መላክ ይኖርባቸዋል፡፡
   - የህጻኑ ስም በማሸጊያዊ ላይ መጻፍ አለበት
   - **የህክምና ባለሙያው በአዲስ መልክ የመድሐኒት አወሳሰድ መንገድን በጽሁፍ እስካልገለጸ ድረስ መጀመሪያ በማሸጊያው ላይ የታተመው የአወሳሰድ ሁኔታ ብቻ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡**

4. በመድሐኒት አወሳሰድ ወይም ዶዝ ላይ የሚደረግ **<u>ማንኛውም</u>** በሚኖርበት ወቅት ይህንኑ ገልጾ ሀኪም ወይም ፋርማሲስት የሚያቀርበው ፈቃድ ከመድሐኒቱ ጋር አብራ ማያያዝ ተገቢነት አለው፡፡

5. የሚመከረው አካሄድ “እንደ አስፈላጊነቱ" በሀኪም ትእዛዝ የሚወሰድ መድሐኒት ቢበዛ የአንድ ሳምንት ወይም ያነሰ ጊዜ ዶዝ ብቻ ይዞ መምጣት ይገባል፡፡ በየ እለቱ የሚወሰዱ መድሐኘቶች እስከ ሰላሳ (30) ቀናት ድረስ የሚያገለግሉ መድሐኒቶችን ተቀብሎ ማስተናገድ ይቻላል፡፡

6. የጤና ባለሙያዎች ከተማሪ ወላጆች እና መምህራን ጋር በመተባበር ተማሪዎች ወደ ህክምና ጽህፈት ቤት በመምጣት በመደበኛነት መድሐኒት እንዲወስዱ ያበረታታሉ፡፡

7. የፓርክ ሂል ስኩል ዲስትሪክት ለተማሪዎች መድሐኒት አያቀርብም፡፡ እነዚህም መድሐኒቶች እንደ አስፐሪን፣ ታይላኖል፣ የሳል ሽሮፕ፣ የሆድ መድሐኒት፣ ሰን ስክሪን እና አንቲ አሲድ ናቸው፡፡

| የተማሪ ስም፡ | የመድሐኚት ስም: |
| --- | --- |
| ዶዝ: | በት/ቤት መድሐኒት መውሰጃ ሰአት: |
| መድሐኒት የሚወሰድበት ምክንያት/ሁኔታ: | |
| ልዩ መመሪያዎች: | |

***ከላይ የጠመለከተውን የመድሐኚት አወሳሰድ መመሪያ አንብቤ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከትምህርት ዘመኑ መጨረሻ በፊት የቀሩ መድሐኚቶችን ቀጥሎ ከተመለከቱት በአንዱ አማራጭ ይረከቡ፣ ወይም በፓርክ ሂል ፖሊሲ እና አሰራር መሰረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡***
***በመጨረሻው የትምህርት ሳምንት:***

☐ ***መድሐኒቱን በልጄ በኩል ይላኩልኝ***
☐ ***በእራሴ መድሐኒቱን መረከብ እመርጣለሁ***
☐ ***ልጄ የሚወሰደው መድሐኒት ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ቅመም መሆኑን በመገንዘብ አዋቂዎች መረከብ እንዳለባቸው እገነዘባለሁ***

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:______________________________ ቀን:______________________